# ፖሊሲ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

ፅሁፎች ግብአቶች፦ ABA, ABARA, ABC-RA, ACG, BFA, BMA, FAA, IEA, IEB, IED, IFB, IGPRA, IRBRA

ሃላፊነት ያለበት ቢሮ: ግንኙነቶች እና የቤተሰብ ተደራሽነት

## የወላጅና የቤተሰብ ተሳትፎ

**A. ዓላማ**

1. **የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) ለተማሪዎች ትምህርታዊ ስኬት አስፈላጊ እንደ ሆነ አካል በማድረግ ትርጉም ያለው የቤተሰብ-ትምህርት ቤት ሽርክናዎችን/አጋርነቶችን ለማሳደግ በቁርጠኝነት ይሰራል።**

2. ቦርዱ የልጆችን ትምህርት፣ ጤናማ እድገት እና ደህንነትን እንዲደግፉ በትምህርት ቤት ማህበረሰብ ውስጥ የወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎን ያበረታታል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የማህበረሰቡን ብዝሃነት የሚያጠቃልሉ የቤተሰብ ተሳትፎ ጥረቶችን ለማበረታታት እርምጃዎችን ይወስዳል።

B. **ጉዳዩ**

ጥናት እንደሚያመለክተው ቤተሰብ በትምህርት ላይ ያለው ተሳትፎ በተማሪ ትምህርት እና ጤናማ እድገት ላይ በጎ ተፅዕኖ አለው እና የውጤት/ስኬት ክፍተቶችን በመቀነስ ረገድ ጠቃሚ ስልት ነው። በተጨማሪም፣ ትርጉም ያላቸው እና ውጤታማ የቤት-ትምህርት ቤት ሽርክናዎች/አጋርነቶች ደህንነቱ የተጠበቀ እና የተከበረ የመማሪያ አካባቢን ለማረጋገጥ ይረዳሉ።

C. **አቋም**

1. ቦርዱ ሁሉን አቀፍ እና ከተማሪ ትምህርት ጋር የተቆራኙ እና ለቤተሰብ-ትምህርት ቤት አጋርነቶች በብሔራዊ መመዘኛዎች ላይ የተመሰረቱ ግን በዚህ ብቻ ያለተወሰኑ የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን ይደግፋል/ያበረታታል።

   a) ሁሉንም ቤተሰቦች ወደ ት/ቤት ማህበረሰብ መቀበል—ቤተሰቦች በትምህርት ቤቱ ህይወት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ናቸው፣ እናም ጥሩ አቀባበል ያገኙ፣ የተከበሩ እና እርስበርስ፣ ከትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ እና ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እየተማሩት እና እያደረጉት ካለው ነገር ጋር ግንኙነት/ቁርኙት እንዳላቸው ሊሰማቸው ይገባል።

   b) ውጤታማ በሆነ መንገድ መግባባት—ቤተሰቦች እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች ስለ ተማሪ ትምህርት መደበኛ እና ትርጉም ያለው የሁለትዮሽ ግንኙነት ያደርጋሉ።

c) የተማሪን ስኬት መደገፍ — ቤተሰቦች እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች የተማሪዎችን ትምህርት እና ጤናማ እድገት በቤት ውስጥ እና በትምህርት ቤት ለመደገፍ ያለማቋረጥ ይተባበራሉ፣ እና ይሄንንም በብቃት ለማከናወን እውቀታቸውን እና ክህሎቶቻቸውን ለማጠናከር መደበኛ/ቋሚ እድሎች አሏቸው።

d) ልጆቻቸውን ወክለው መናገር—ቤተሰቦች ለልጆቻቸው ጥብቅና እንዲቆሙ፣ ተማሪዎች በፍትሃዊነት እንዲስተናገዱ እና ስኬታቸውን የሚደግፉ የመማር እድሎች እንዲኖራቸው ለማድረግ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል።

e) ስልጣንን መጋራት—ቤተሰቦች እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች በልጆች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ውሳኔዎችን በተመለከተ ልዩ መረጃ ያላቸው አስፈላጊ እና ዋጋ ያላቸው አጋሮች ናቸው። ቤተሰቦች እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች በአንድነት/በጋር በትምህርት ቤት መሻሻል ሂደት ውስጥ ሙሉ ተሳትፎን ጨምሮ ፖሊሲዎችን፣ ልምዶችን እና ፕሮግራሞችን ያሳውቃሉ፣ ተፅዕኖ ያደርጋሉ እና ይፈጥራሉ።

f) ከማህበረሰቡ ጋር መተባበር—ቤተሰቦች እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች ከማህበረሰብ አባላት ጋር በመተባበር ተማሪዎችን፣ ቤተሰቦችን እና ሰራተኞችን ጋር በማገናኘት/በማስተሳሰር የትምህርት እድሎች፣ የማህበረሰብ አገልግሎቶች እና የሲቪክ ተሳትፎን ለማስፋፋት ይሰራሉ።

2. ሁሉም የMCPS ሰራተኞች ለወላጅ እና ለቤተሰብ ተሳትፎ ያላቸውን ቁርጠኝነት ማስተዋወቅ እና ማሳየት ይጠበቅባቸዋል።

D. **ተፈላጊው ውጤት**

**ጠንካራ የቤተሰብ-ትምህርት ቤት አጋርነቶችን ለመገንባት ሁሉም የMCPS ሰራተኞች ከቤተሰቦች ጋር በትብብር ይሰራሉ።**

E. **የአተገባበር ስልቶች**

1. የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የነበሩትን ፖሊሲዎች እና አሰራር ሂደቶችን ይገመግማል/ትገመግማለች፣ እና ይሄንን ፖሊሲ ለመደገፍ አስፈላጊ ደንቦችን እና ሂደቶችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች።

2. የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ እና የትምህርት ቦርድ ከግብ 3 ጋር የተገናኙትን ወሳኝ ደረጃዎች እና የመረጃ ነጥቦችን ይቆጣጠራሉ፦ በMCPS ስልታዊ ዕቅድ ውስጥ ለትምህርት ስኬታማ አጋርነቶችን ማጠናከር።

3. **ቦርዱ በቦርድ ስብሰባዎች ላይ በህዝባዊ አስተያየቶች፣ በጽሁፍ እና በኢሜል መልእክቶች፣ በአማካሪ ኮሚቴዎች አገልግሎት እና በህዝብ ችሎቶች እና በማህበረሰብ መድረኮች ላይ በመሳተፍ አስተያየት እንዲሰጡ ለወላጆች እና ለሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች እድሎችን ይሰጣል። የት/ቤት ስርዓት ፖሊሲዎችን ከማዘጋጀት እና ከመከለስ ሂደቶች፣ ስልታዊ እቅድ ማውጣት፣ የበጀት ልማት/ዝግጅት እና የት/ቤት ዲስትሪክት ጅማሮዎችን ትግበራ በሚመለከት ብዝሀነት ካለው ማህበረሰባችን የሚመጡ ልዩ ልዩ አስተያየቶች ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ።**

**F. ግምገማ እና ሪፖርት**

**ይህ ፖሊሲ የሚገመገመው በትምህርት ቦርድ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት መሰረት ነው።**

የፖሊሲ ታሪክ: በኖቬምበር 13፣ 1990 ውሳኔ ቁጥር 66990 ተቀባይነት አግኝቷል፤ በሴፕቴምበር 1996 ተሻሽሏል፤ በውሳኔ ቁጥር 489-02፣ ኦክቶበር 28፣ 2002 ማሻሻያ ተደርጎበታል፣ በውሳኔ ቁጥር 417-10፣ ጁላይ 26፣ 2010 ማሻሻያ ተደርጎበታል።